የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፱
አዲስ አበባ ጥር ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No. 9
ADDIS ABABA, 3rd February, 2023


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፪/፪ሺ፲፭

ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ

ገጽ……………………………….፲፬ሺ፮፻፱


## Content


Proclamation No. 1282/2023

National Payment System (Amendment) Proclamation……..............................Page14609


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፪/፪ሺ፲፭

## ብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ

በብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት ዉስጥ የተደረጉ ለውጦችን፣ እድገቶችና መሻሻሎችን ታሳቢ በማድረግ የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፰/፪ሺ፩ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፪/፪ሺ፲፭“ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ማሻሻያ

የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፰/፪ሺ፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

## PROCLAMATION NO.1282/2023

## NATIONAL PAYMENT SYSTEM (AMENDMENT) PROCLAMATION

**WHEREAS**, it has become necessary to amend the National Payment System Proclamation No. 718/2011 in line with new developments, changes and innovations in the National Payment System;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the “National Payment System (Amendment) Proclamation No 1282/2023”.

### 2. Amendment

The National Payment System Proclamation No. 718/2011 is hereby amended as follows:

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ—አንቀጽ (፬)፣ (፲፪)፣ (፲፰) እና (፳) ተሰርዞ በሚከተለዉ አዲስ ንዑስ-አንቀጽ (፬)፣ (፲፪)፣ (፲፰) እና (፳) ተተክቷል፡፡

“፬/ **“የመንግሥት ሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት”** ማለት፡-

ሀ/ የመንግሥት ሰነደ ሙዓለ-ንዋዮች ወጥነት ባለዉ መልኩ የሚከማቹበት ወይም ወደ ኤሌክትሮኒክ ይዘት ተቀይረዉ የሚቀመጡበት ወይም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በመንግሥት የሚመዘገቡበት ሆኖ እነዚህ ሰነደ ሙዓለ-ንዋዮችን በተመለከተ የሚደረግ ግብይት ሰነዶቹን በአካል ማረካከብ ሳያስፈልግ የሰነዶቹ መተሳሰቢያ መዝገብ ላይ ብቻ በሚደረግ ወጪና ገቢ ለማስተላለፍ የሚያስችል ሥርዓት ነዉ፤

ለ/ በመንግሥት ሰነደ ሙዓለ-ንዋዮች ግብይት ሂደት ወቅት የሰነዶች ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ፣ ክፍያ ማጣራት፣ ርክክብ እና ማወራረድ ያለ አካላዊ ቅብብል ለማከናወን የሚያስችል ወይም ግብይቱን የሚያሳልጥ ዘዴ ወይም ሥርዓት፤ እና ሌሎች ተያያዥ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሥርዓት ነው፡፡

፲፪/ **“የፋይናንስ ተቋም”** ማለት ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የመድን ሰጪ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ፣ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር፣ የሐዋላ ድርጅት፣ የፖስታ ቁጠባ፣ ወይም በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ተቋም ነው፤

1/ Sub-Articles (4), (12), (18) and (20) of Article 2 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub Articles (4), (12), (18) and (20).

“(4) “**Central Security Depository for Government Securities**” means a system:

a) where government securities are immobilized or dematerialized and held in the government custody by, or registered in the name of government for depositors and dealing in respect of government securities are effected by means of entries in the securities accounts without the physical delivery of certificates;

b) which permits or facilitates the registration, clearing and settlement of government securities transactions or dealings in securities without the physical delivery of certificates.

12/ **“Financial Institution”** means a bank, a microfinance institution, an insurance company, a re-insurer, a payment instrument issuer, a payment system operator, a money transfer institution, a postal saving or such other similar institution as may be determined by the National Bank;

፲፱/ **“የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር”** ማለት ብሔራዊ ባንክ፣ የፋይናንስ ተቋም፣ ወይም የክፍያ ትእዛዝን ወይም የመንግሥት ሰነደ ሙዓለ-ንዋዮችን የሚያስተላልፍ፣ የሚያቻችል፣ የሚያጣራ፣ የተጣራ የመጨረሻ ተከፋይ ሂሳብን የሚወስን እና የሚያወራርድ ስርዓትን እንዲያቋቁምና እንዲሰራ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ወይም ይሁንታ የሰጠው ሌላ ማንኛውም ኩባንያ ነው፤

፳/ **“የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ”** ማለት አንድ ሰው የኢትዮጵያን ብር በሚስተካከል ገንዘብ ለሚከፍለው ክፍያ በልዋጭ የሚሰጠው ሰነድ ሲሆን ገንዘብ፣ ዕቃ ወይም አገልግሎት እንዲያገኝ ወይም ክፍያ እንዲፈፅም የሚያስችለው ግዙፍነት ያለውም ሆነ የሌለው ማናቸውም የኤሌትሮኒክ ገንዘብንና፣ ካርድን የሚጨምር ነዉ፤”

፪./ ከአዋጁ ከአንቀጽ ፪ ንዕስ-አንቀጽ (፳፰) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፳፱)፣ (፴)፣ (፴፩)፣ (፴፪)፣ (፴፫)፣ (፴፬)፣ (፴፭)፣ (፴፮) እና (፴፯) ተጨምረዉ ነባሩ ንዕስ- አንቀጽ (፳፱) ንዑስ-አንቀጽ (፴፰) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

“፳፱/ **"የውጭ ሀገር ገንዘብ"** ማለት ከኢትዮጵያ ገንዘብ በስተቀር ከኢትዮጵያ ውጭ በማናቸውም ሀገር ሕጋዊ ገንዘብ የሆነና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረግ ክፍያ ተቀባይነት እንዳለው ብሔራዊ ባንክ ያሳወቀው ማናቸውም ገንዘብ ነው፤

18/ “**Payment System Operator**” means the National Bank, a financial institution, or any other company licensed or authorized by the National Bank to establish and operate a payment system including routing, matching, clearing, netting, and settlement of payment instructions or government securities;

20/ “**Payment Instrument**” means any instrument, whether tangible or intangible which is issued against the receipt of fund equivalent in Ethiopian Birr, that enables a person to obtain money, goods or services or to otherwise make payments which include electronic money and cards; ”

2/ The following new Sub-Articles (29), (30), (31), (32), (33), (34), (35), (36) and (37) are added following Sub-Article (28) of Article 2 of the Proclamation and the existing Sub-Article (29) is re-numbered as Sub-Article (38) .

“29/ "**Foreign Currency**" means any currency other than Ethiopian legal tender which is legal tender in any country outside Ethiopia as to which the National Bank has declared to be acceptable for payment in Ethiopia;

፴/ "**ኩባንያ**" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተገለጸው የአክሲዮን ማህበር ሲሆን በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና ጽሕፈት ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ ነው፤

፴፩/ "**ኤሌክትሮኒክ ገንዘብ**" ማለት አውጪው የሚገደድበት በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ወይም በሌላ የክፍያ መፈጸሚያ መሣሪያ ዉስጥ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የተከማቸ፣ ከኢትዮጵያ ብር ጋር እኩል በሆነ መልኩ የሚፈጠር፣ ከአዉጪዉ ዉጪ ባሉት አካላት ለክፍያ ተቀባይነት ያለዉ፣ የክፍያ መፈጸሚያ የሆነ እና ወደ ጥሬ ገንዘብ መለወጥ የሚችል የገንዘብ እሴት ነዉ፤

፴፪/ **"የውጭ ሀገር ዜጋ"** ማለት የኢትዮጵያ ዜጋ ያልሆነ ሰው ነው፤

፴፫/ "**ተቀጥላ**" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ የተሰጠዉን ትርጓሜ የያዘ ሆኖ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመዘገበና ዋና ጽሕፈት ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ በቴሌኮም ኩባንያ፣ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ወይም በክፍያ ሥርዓት ኦፐሬተር ቁጥጥር ስር ያለ የንግድ ማህበር ነዉ፤

፴፬/ **"የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ"** ማለት በብሔራዊ ባንክ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ እንዲያወጣ ፈቃድ የተሰጠው ኩባንያ ወይም በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ወይም ይሁንታ የተሰጠው ባንክ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም ነው፤

30/ "**Company**" means a share company as defined under the Commercial Code of Ethiopia and registered under the laws of, and having its head office in Ethiopia;

31/ "**Electronic Money**" means monetary value as represented by a claim on its issuer, that is electronically stored in a payment instrument or electronic equipment, issued against receipt of fund equivalent in Ethiopian Birr, accepted as means of payment by persons other than the issuer and can be redeemed in cash;

32/ "**Foreign National**" means a person who is not an Ethiopian national;

33/ "**Subsidiary**" means a business organization as defined under the Commercial Code of Ethiopia controlled by a telecom operator, a payment instrument issuer or a payment system operator and registered under the laws of, and having its head office in Ethiopia;

34/ "**Payment Instrument Issuer**" means a company or a government owned enterprise licensed by the National Bank or a bank or a microfinance institution authorized by the National Bank to issue payment instruments;

፴፭/ "**ይሁንታ**" ማለት ከብሔራዊ ባንክ በሌላ የፋይናንስ አገልግሎት ፍቃድ አግኝቶ በተጨማሪ በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አዉጪነት ወይም በክፍያ ስርዓት ኦፐሬተርነት የሥራ ዘርፍ ለመሰማራት ብሔራዊ ባንክን ሲጠይቅ የሚጸድቅበት አሠራር ነዉ፤

፴፮/ "**ኢንቨስትመንት ከለላ ክፍያ**" ማለት የውጪ ሀገር ዜጎች ለሀገር ዉስጥ ባለሃብቶች ብቻ በተፈቀደ የሥራ ዘርፍ ዉስጥ ለመሰማራት ለመንግስት የሚከፈል ክፍያ ነዉ፤

፴፯/ "**በውጪ አካላት ማሠራት**" ማለት አንድ የፋይናንስ ተቋም የራሱን የዉስጥ ሥራ(ዎች) ከተቋሙ ውጪ ባለ አካል ማሠራት ማለት ነዉ፤"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ(፩) ፊደል ተራ (ለ)፣ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ለ) ተተክቷል፡

"(ለ) የመንግስት ሰነደ ሙዓለ-ንዋይ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት፤"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) እና (መ) ተሰርዘው በሚከተለዉ አዲስ ፊደል ተራ (ሀ) እና (መ) ተተክተዋል፡፡

"ሀ) ለሚከተሉት ሰዎች ፈቃድ ወይም ይሁንታ የመስጠት

I. ለክፍያ ሥርዓት ኦፐሬተር፣ እና

II. ለክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ፤

መ) ለተሳታፊዎች፣ ለክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪዎችና የክፍያ ሥርዓት ኦፐሬተሮች፤

I. የክፍያ ሥርዓት መሠረተ ልማቶችን ለመገንባትና እርስ በርሳቸውም ተናባቢ እንዲሆኑ ለማድረግ

35/ "**Authorization**" means a process by which the National Bank approves the application of a financial institution, which is already licensed by the National Bank to provide financial services, to become a payment instrument issuer or a payment system operator;

36/ "**Investment Protection Fee**" means an amount paid to the government by foreign nationals who invest in businesses that are reserved to domestic investors only;

37/ "**Outsourcing**" means a process by which a financial institution hires an external body to perform its own internal task(s); "

3/. Paragraphs (b) Sub-Article (1) of Article 4 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new paragraphs (b);

"b/ central security depository for government securities;"

4/ Paragraphs (a) and (d) of Sub-Article (2) of Article 4 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Paragraphs (a) and (d).

"a) license or authorize:

I. a payment system operator; and

II. a payment instrument issuer;"

d) prescribe to participants, payment instrument issuers and operators by Directive on;

I. investments in relation to building system infrastructure and system interoperability;

የሚያስፈልጋቸውን ኢንቨስትመንት፤

II. ወጪ ስለሚጋሩበት ሁኔታ፤

III. ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያስከፍሉትን ክፍያ፤

IV. በኤሌክትሮኒክ ሒሳብ ውስጥ የሚኖርን የገንዘብ ጣሪያ፣ በኤሌክትሮኒክ ሒሳብ አማካኝነት ለሚፈጸም ግብይት፣ እና ከወኪል እና ከሌላ ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ወጪ የሚደረግን የጥሬ ገንዘብ ጣሪያን

በመመሪያ የመወሰን፡፡”

፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፭ ተሠርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀጽ ፭ ተተክቷል፡፡

“፭. **ስለ ፈቃድ፣ ይሁንታ እና ክልከላ**

፩/ ከብሔራዊ ባንክ በስተቀር ሌላ ማንኛውም ሰው ከባንኩ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ሳያገኝ የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር መሆን አይችልም፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፷፭/፪ሺ፪ ለሚያከናውነው የፋይናንስ አገልግሎት ተግባር በዚህ አዋጅ መሠረት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የማግኘትና ባንኩ በዚህ ረገድ ለሚያካሂዳቸው አስፈላጊ የቁጥጥርና ክትትል ሥራዎችም ተገዢ መሆን አለበት፡፡

II. cost sharing;

III. charges for the service they provide;

IV. maximum limits on electronic account balance, transaction and cash withdrawal at agent and electronic equipment.”

5/ Article 5 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 5.

“5. **Licensing, Authorization and Prohibition**

1/ No person except the National Bank may be a payment system operator or issuer of payment instrument unless such person is licensed or authorized by the National Bank.

2/ The Ethiopian Postal Service Enterprise, in its financial services activities as regulated by Council of Ministers Regulation No. 165/2009, shall be subject to the duty of obtaining an authorization and to any oversight requirements imposed by the National Bank under this Proclamation.

፫/ ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሁፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ማናቸውም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ወይም የክፍያ መፈፀሚያ ሰነድ አውጪ፡-

(ሀ) አዲስ ሥርዓት በሥራ ላይ ማዋል ወይም አዲስ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነዶችን ማውጣት፣

(ለ) ከሌላ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ጋር መዋሃድ ወይም የሌላ ሰው የክፍያ ሥርዓት ባለቤትነት መረከብ፤

(ሐ) በመቀላቀልም ሆነ በሌላ መንገድ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተሩን ሥራ መሸጥ ወይም ባለቤትነትን የሚያስቀሩ ማናቸውንም ዓይነት ስምምነቶች ወይም ውሎች መፈፀም ወይም በሥራ ዘርፉ ላይ ዓይነተኛ ለውጥ ማድረግ፤

(መ) አክሲዮኑን መልሶ መግዛት ወይም በመደበኛ ተግባሩ በተከሰተ ኪሣራ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ካፒታሉን መቀነስ፤

(ሠ) የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻል፤ ወይም

(ረ) የክፍያ ሥርዓቱን የሚያካሂድበትን የንግድ ስም መቀየር፤ አይችልም፡፡

፬/ ብሔራዊ ባንክ አንድ የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርን ሥራውን ከማከናወን ወይም የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪን ሰነድ ከማውጣት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ በጽሁፍ ሊከለክል ይችላል፤

(ሀ) አንድ የክፍያ ሥርዓት ወይም የክፍያ መፈጸሚያ መሳሪያ ለብሔራዊ የክፍያ ሥርዓቱ አስተማማኝነት፣ ደህንነት፣ ቀልጣፋነት እና ማሳለጥ ጎጂ ከሆነ፤ ወይም

3/ Without the prior written approval of the National Bank, no payment system operator or payment instrument issuer may:

(a) introduce new system or issue new payment instrument;

(b) merge with or take over a system of another operator;

(c) enter into any arrangement or agreement for the sale or disposal, by amalgamation or otherwise, of its business, or effect major changes in its line of business;

(d) redeem its own shares or effect a reduction of its capital other than through reduction due to operating losses;

(e) amend its memorandum of association; or

(f) alter the name under which it is authorized to operate a system.

4/ The National Bank may prohibit in writing, payment system operator or payment instrument issuer from operating any system or issuing payment instrument where:

a) the system or payment instrument is detrimental to the reliable, safe, efficient and smooth operation of the national payment system; or

(ለ) ክልከላው የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፡፡

፭/ የክፍያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር በማንኛውም ጊዜ አግባብነት ያላቸውን በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኛን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጡ የሀገሪቱን ሕጎች ማክበር እና መተግበር ይኖርበታል፡፡”

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፮ ተሠርዞ በሚከተለዉ አዲስ አንቀጽ ፮ ተተክቷል፡፡

“፮. <u>ፈቃድ ወይም ይሁንታ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

፩/ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ፈቃድ ለማግኘት ማመልከቻ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ ባንክ ወይም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ ለማውጣት ይሁንታ ለማግኘት ማመልከቻ ለብሔራዊ ባንክ ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ ከፋይናንስ ተቋም እና በመንግስት ባለቤትነት ከተያዘ ድርጅት ውጭ ያለ የንግድ ማህበር የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ፈቃድ ማውጣት ከፈለገ ለዚሁ ዓላማ ብቻ የሚያገለግል ተቀጥላ ኩባንያ ማቋቋም አለበት፡፡

፬/ ብሔራዊ ባንክ ተቀጥላ ኩባንያ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

b) the prohibition is otherwise in the interest of the public.

5/ A payment instrument issuer or payment system operator shall always apply on Prevention and Suppression of Money Laundering and Financing of Terrorism legislations of the country.”

6/Article 6 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 6.

“ 6. **<u>Application for License or Authorization</u>**

1/ Application for license to be a payment instrument issuer or payment system operator shall be submitted to the National Bank.

2/ A bank or a microfinance institution shall submit application for authorization to the National Bank to issue payment instruments.

3/ A business organization other than financial institution and government owned enterprise intending to be licensed as a payment instrument issuer or a payment system operator shall establish a subsidiary company exclusively for the purpose.

4/ The National Bank may prescribe by a Directive conditions in relation to establishment of a subsidiary company.

፭/ በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነት ሥራ ዘርፍ እንዲሰማራ የሚፈቅድ ልዩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ሊኖረው ይገባል፡፡

፮/ ለክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት እና ለክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነት ማመልከቻ የሚያቀርብ አመልካች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰነውን ዝቅተኛውን የተከፈለ ካፒታል ማሟላት አለበት፡፡

፯/ የውጭ ሀገር ዜጎች በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነት ስራ ዘርፍ ሊሰማሩ ይችላሉ፣ ወይም በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነት ፈቃድ የሚሠራ ተቀጥላ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

፰/ የውጭ ሀገር ዜጎችና ሙሉ በሙሉ በውጭ ሀገር ዜጎች ባለቤትነት የተያዙ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነት ሥራ ዘርፍ የሚሰማሩት የሚፈለገዉ ካፒታል ሙሉ በሙሉ በውጭ ምንዛሬ የተከፈለ ከሆነ ነው ፡፡

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፰) የተገለጸው ቢኖርም በከፊል በውጭ ሀገር ዜጎች ባለቤትነት የተያዘ ኢትዮጵያዊ ድርጅት በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪነት ወይም በክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነት ሥራ ዘርፍ የሚሰማራው የኩባንያዉን ካፒታል ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በድርጅቱ በውጭ ሀገር ዜጎች የተያዘው ጠቅላላ ድርሻ በመቶኛ ተሰልቶ በውጭ ምንዛሪ የተከፈለ ከሆነ ነው፡፡

5/ A government owned enterprise shall have a specific Regulation issued by the Council of Ministers that allows the enterprise to engage in a payment instrument issuer or a payment system operator business.

6/ An applicant for payment instrument issuer and payment system operator shall fulfill minimum paid up capital as may be prescribed by the National Bank Directive.

7/ Foreign nationals may be allowed to engage in a payment instrument issuer or a payment system operator business; or establish a subsidiary which shall be licensed as a payment instrument issuer or payment system operator.

8/ Foreign Nationals and Ethiopian organizations fully owned by foreign nationals shall engage in a payment instrument issuer and/or payment system operator business through raising capital fully paid in foreign currency.

9/ Notwithstanding Sub-Article (8) of this Article, Ethiopian organizations partially owned by foreign nationals shall, according to aggregate percentage holding by foreign nationals as may be prescribed by the National Bank Directive, invest in a payment instrument issuer or payment system operator business in an acceptable foreign currency.

፲/ ብሔራዊ ባንክ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በውጭ ሀገር ዜጎች የተያዘ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ሥራውን በዉጭ ሀገር ዜጎች ስለሚያሠራበት፣ ሥራውን በዉጭ አካላት ስለሚያሠራበት፣ እንዲሁም በእናት ኩባንያ እና በተቀጥላ መካከል ስለሚኖር ግንኙነት ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

፲፩/ የሥራ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ለማግኘት የሚቀርብ አመልካች በብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰነውን ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

፲፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፲፩) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዉጪ ሀገር ዜጎች በክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም በክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ሥራ ውስጥ ሲገቡ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረት ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ከለላ ክፍያን በውጭ ምንዛሬ ሊያስከፍል ይችላል፡፡

፲፫/ ብሔራዊ ባንክ ማመልከቻው እንደደረሰው በጥያቄው ላይ መወሰን እንዲያስችለው አመልካቹ ስላቀረበው ዝርዝር መረጃ ትክክለኛነት፣ የክፍያ ሥርዓቱን ለማከናወን ስላለው ብቃት፣ የሥርዓቱ ተሳታፊዎች ስላቀረቧቸው የብቃት ማረጋገጫዎች፣ እንዲሁም ስለሌላ ማናቸውም ከማመልከቻው ጋር ስለተያያዘ ጉዳይ አስፈላጊ የመሰለውን ማጣራት ሊያደርግ ይችላል፡፡

10/ The National Bank may prescribe by a Directive conditions in relation to employment of expats, outsourcing and relationship between parent company and subsidiary of a payment instrument issuer or a payment system operator fully or partially owned by foreign nationals.

11/ An applicant for license or authorization shall pay licensing or authorization fee as may be prescribed by the National Bank Directive.

12/ Notwithstanding Sub-Article (11) of this Article a new foreign entrant into the payment instrument issuer or payment system operator business may be required to pay investment protection fee in foreign currency for joining protected sector as may be prescribed by the National Bank Directive.

13/ After the receipt of application, the National Bank may make such inquiries as it may consider necessary for the purpose of satisfying itself about the genuineness of the particulars furnished by the applicant, his capacity to operate a system, the credentials of the participants of the applicant's system and any other matter related to the application.

፲፬/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (፲፫) የተመለከተውን ማጣራት ካደረገ በኋላ የቀረበው ማመልከቻ የተሟላና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በባንኩ የወጡ መመሪያዎችን የተከተለ መሆኑን ሲያምንበት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ለሥርዓቱ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ይሰጣል፡-

(ሀ) የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተሩ ወይም የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አዉጪዉ ለማቋቋም ያቀደው ሥርዓት ወይም ለመስጠት ያቀደው አገልግሎት ተፈላጊነት፤

(ለ) የታቀደው ሥርዓት የቴክኒክ ደረጃና የአሠራር ንድፍ፤

(ሐ) የደህንነት መመሪያዎችን ጨምሮ የታቀደው ሥርዓት የሚመራባቸው ዝርዝር ሁኔታዎች፤

(መ) የሒሣብ ማጣራትና ማቻቻል ዝርዝር ሁኔታዎችን ጨምሮ በሥርዓቱ ገንዘብ የሚተላለፍበትን ሁኔታ፤

(ሠ) የአመልካቹ የፋይናንስ አቋም፣ የማስተዳደር ልምድ እና ታማኝነት፤

(ረ) የተገልጋዮች ጥቅም የሚከበርበትና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከኦፕሬተሩ ወይም ከክፍያ ሰነድ አዉጪዉ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሚገዛበት ዝርዝር ሁኔታ፤

14/ The National Bank may, if satisfied, after an inquiry under Sub-Article (13) of this Article, that the application is complete and conforms to the provisions of this Proclamation and Directives issued by the National Bank, issue a license or an authorization for operating the system under this Proclamation having regard to the following considerations:

(a) the need for the proposed system or the service proposed to be undertaken by the payment system operator or payment instrument issuer;

(b) the technical standards or the design of the proposed system;

(c) the terms and conditions of operation of the proposed system, including any security procedure;

(d) the manner in which transfers may be effected within the system, including specifications on clearing and netting procedures.

(e) the financial status, experience of management and integrity of the applicant;

(f) interests of consumers, including the terms and conditions governing their

(ሰ) በገንዘብና ብድር ፖሊሲ ላይ ስለሚኖረው ፋይዳ፤ እና

(ሸ) ከብሔራዊ የክፍያ ሥርዓት ጋር በተያያዘ አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ሌሎች ሁኔታዎች፡፡

፲፭/ ብሔራዊ ባንክ ከአመልካቹ የሚፈለጉ መረጃዎች ተሟልተው ከቀረቡበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፷ (ሥድሳ) ቀናት ውስጥ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (፩) መሠረት በቀረበ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፲፮/ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው ማቅረብ ያለበትን አስፈላጊ መረጃዎች እና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡"

፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፩ ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ አንቀጾች ከአንቀጽ ፴፪ እስከ ፴፰ ተጨምረዉ ነባር አንቀጾች ከአንቀጽ ፴፱ እስከ ፵፮ ሆነዉ ተሸጋሽገዋል፡፡

"፴፪. <u>ስለ ክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪና የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ዳይሬክተሮችና የሥራ አስፈጻሚዎች</u>

፩/ ክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጭነት ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተርነት ሥራ ፍቃድ በሚሰጥበት ጊዜም ሆነ በሌላ በማናቸውም ጊዜ የሚደረግ የማናቸውም የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር

relationship with payment system operator or payment instrument issuer, when relevant;

(g) the impact on monetary and credit policies; and

(h) such other factors as it may consider relevant in relation to the national payment system.

15/ The National Bank shall respond to the application submitted in accordance with Sub-Article (1) of this Article within 60 (Sixty) days of submission of all required information.

16/ The National Bank may provide by Directive information to be submitted by the applicant and other conditions required for licensing or authorization."

7/ The new Articles 32 to 38 are added after Article 31 of the Proclamation; and the existing Articles 32 to 39 of the Proclamation are renumbered as Articles 39 to 46.

"**32**. **<u>Board of Directors and Executive Officers of the Payment Instrument Issuers or Payment System Operator</u>**

1/ Appointment of any Director, Chief Executive Officer of a payment instrument issuer or payment system operator at the time of licensing or at any other time may not be valid unless

ዳይሬክተር ወይም የስራ አስፈፃሚ ሹመት በብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ካልጸደቀ በቀር በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፪/ የፋይናንስ ተቋም ዳይሬክተር ወይም የሥራ አስፈጻም በተመሳሳይ ጊዜ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ዳይሬክተር ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ ባንክ የመድን ኩባንያ ወይም የጠለፋ መድን ኩባንያ ዳይሬክተር በተመሳሳይ ጊዜ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ዳይሬክተር የሚሆንበትን አግባብ በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

**፴፫. <u>የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ እና የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር ተግባራት</u>**

፩/ በብሔራዊ ባንክ በጽሑፍ ሲጸድቅለት የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ኦቨርድራፍትን ጨምሮ አነስተኛ ብድር፣ አነስተኛ ቁጠባ፣ አነስተኛ መድን፣ ወደ ሀገር የሚላክ ዓለምአቀፍ ሐዋላ ወይም ሌላ ተዛማጅ አገልግሎት እንዲሰጥ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ከሰጠዉ የፋይናንስ ተቋም ጋር በመሆን በዲጂታል ዘዴ ማሳለጥ ይችላል፡፡

፪/ ብሔራዊ ባንክ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተገለጹትን አገልግሎቶች ለመስጠት መሟላት ያለባቸውን ዝቅተኛ መስፈርት እና ቅድመ ሁኔታ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

written approval is granted by the National Bank.

2/ A Director or Chief Executive Officer of a financial institution may not, at the same time, serve as a Director of a payment instrument issuer or a payment system operator.

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article the National Bank may , by a Directive, put conditions on the appointment of the Director of an insurance company or a re-insurer to be, at the same time, a Director for a payment instrument issuer or payment system operator.

**33. <u>Activities of Payment Instrument Issuer and Payment System Operator</u>**

1/ Up on a written approval of the National Bank, a payment instrument issuer may facilitate the provision of micro credit including overdraft, micro saving, micro insurance, inward international remittance or any other related services digitally in partnership with a Financial Institution licensed by the National Bank.

2/ The National Bank may provide by Directive minimum requirements and conditions to provide facilitation service stated under Sub-Article (1) of this Article.

**፴፬. ድንበር ተሻጋሪ ክፍያዎች**

፩/ ብሔራዊ ባንክ ክፍያዎችን ለማስተላለፍ፣ ለማጣራት፣ ለመክፈል፣ ለማስተዳደር በሚያስችል ድንበር ተሻጋሪ የክፍያ ሥርዓት መዋቅር ዉስጥ ሊሳተፍ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ላይ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም ሰው ድንበር ተሻጋሪ ክፍያዎችን ለማስተላለፍ፣ ለማጣራት፣ ለመክፈል፣ ለመሳተፍ እና ለማስተዳደር በሚያስችል የኦፕሬሽን ወይም የሥርዓት መዋቅር ውስጥ ያለብሔራዊ ባንክ ይሁንታ መግባት አይችልም፡፡

፫/ ድንበር ተሻጋሪ ክፍያዎችን ከማስተላለፍ፣ ከማጣራት፣ ከመክፈል፣ ከመሳተፍ፣ እና ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፴፭. ከሀገር ዉስጥ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም-አቀፋዊ ተቆጣጣሪ ተቋማት ጋር ስለመተባበርና በጋራ ስለመስራት**

ብሔራዊ ባንክ መረጃ ለመለዋወጥ እና በብሔራዊ የክፍያ ሥርዓቱ ላይ የተቀናጀ ክትትል ለማድረግ ብሎም የብሔራዊ ክፍያ ሥርዓቱን አስተማማኝነትና ውጤታማነት ለማረጋገጥ ከሀገር ውስጥ፣ ከቀጠናዊ እና ዓለም-አቀፋዊ ተቆጣጣሪ አካላት ጋር በጋራ ሊሰራ ይችላል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የጋራ አሠራር ምስጢራዊ መረጃዎች የሚጠበቁበትን ሁኔታ ማካተት አለበት፡፡

**34. Cross – Border Payments**

1/ National Bank may enter into any operational or system arrangement for the purpose of routing, clearing, settlement, participation and management of cross – border payments.

2/ Notwithstanding Sub – Article (1) of this Article no person shall enter in to operational or system arrangement for the purpose of routing, clearing, settlement, participation and management of cross – border payments without the written authorization of the National Bank.

3/ The National Bank may issue a Directive on matters related to the operation, routing, clearing, settlement, participation and management of cross – border payments.

**35. Cooperation and Collaboration with Local, Regional and International Regulatory Authorities**

The National Bank may collaborate with relevant Domestic, Regional and International regulatory bodies for information exchange and coordinated oversight of the payment system with the prime objective of ensuring the safety and efficiency of the national payment system. Such collaboration shall include protection of confidential information.

**፴፮. ዓለም-አቀፍ የክፍያ ሥርዓት መርሆችንና እስታንዳርዶችን የራስ አድርጎ ስለመደንገግ**

ብሔራዊ ባንክ የብሔራዊ የክፍያ ሥርዓቱን ደህንነት፣ ውጤታማነትና አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ለክፍያ ሥርዓት ተገቢነት ያላቸውን ዓለም-አቀፍ መርሆችንና እስታንዳርዶችን በመመሪያ የራሱ አድርጎ ሊደነግግ ይችላል፡፡

**፴፯. ፈቃድን ስለማደስ**

፩/ ፈቃድ የተሰጠዉ የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ወይም የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር በየዓመቱ ፈቃዱን ማደስ አለበት፡፡

፪/ ብሔራዊ ባንክ ፍቃድ ስለማደስ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

**፴፰. ተፈጻሚ ድንጋጌዎች**

የአዋጁ አንቀጽ ፯፣ ፰፣ ፱፣ ፲፩፣ ፲፰ እና ፳፮ ድንጋጌዎች እንደነገሩ ሁኔታ ለክፍያ መፈጸሚያ ሰነድ አውጪ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡”

**፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፳፮ ቀን ፪ሺ፲፭ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**36. Adopting Relevant International Payment System Principles and Standards**

The National Bank may issue a Directive to adopt relevant international principles and standards on payment systems to enhance the safety, efficiency and reliability of the national payment system.

**37. Renewal of License**

1/ A licensed payment instrument issuer or a payment system operator shall renew its license in every year.

2/ The National Bank shall issue Directive on conditions of renewal of the license.

**38. Applicable Provisions**

Provisions of Articles 7, 8, 9, 11, 18 and 26 of the Proclamation shall, mutatis mutandis, apply to a licensed or authorized payment instrument issuer.”

**3. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 3rd Day of February, 2023.**

**SAHLE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**